

# የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆነችው ቤተክርስቲያን አካል መሆን

# መግቢያ

ህይወት ጉዞ ነው። እግዚአብሔር ይወድሀል፤በዚህ በህይወት ጉዞ ውስጥ ስኬታማ እንድትሆን ይፈልጋል።ስኬት አንተን ጨምሮ በማንኛውም ሰው ህይወት ውስጥ አስደናቂውን የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትህ በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም ይወሰናል።በመረጥከው መንገድ ላይ በመሆን፤በዘለዓለማዊ መንግስቱ ውስጥ የተትረፈረፈውን በረከት እየተካፈልክ ልትፈጽም ትችላለህ ወይም በአንጻሩ ማለቂያ በሌለው ቅዠት ውስጥ ትኖራለህ።ብሩህ የሆነውን መንገድ መርጠህ የእግዚአብሔርን ዓላማ ትፈጽም ዘንድ በየዕለት ህይወትህ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ይኖርብሀል።ለዚህ ነው ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አንተን ለመርዳት የተዘጋጀው።

እያንዳንዱ ሦስት የትምህርት ክፍሎች አሉት: {1}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤ {2}መሠረታዊ ጥያቄዎች፤እና {3}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማወቅ እንድታድግ ይረዱሀል።መሠረታዊ ጥያቄዎች ደግሞ በምታውቀው የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንድትኖር ይረዳሀል።የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ የቃሉን እውነት በልብህ እንድትሰውር ይረዳሀል።

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ስለሆነችው ቤተክርስቲያን በሚገባ ትማር ዘንድ ይረዱሀል።በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የሚኖረው ማን ነው የሚለውን፤እንዲሁም የእሷ አካል ስለመሆን እና ስለ መንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት ትማራለህ።

እያንዳንዱን ትምህርት በጸሎት ጀምር።መልሶቹን በራስህ አገላለጽ ጻፋቸው።በተገለጠልህ እውነት በሚገባ ትመላለስ እና ትኖር ዘንድ  እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ። እግዚአብሔር እሱን በማወቅ ይባርክህ።

<u>ማስታወሻ</u>: አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መደበኛ ትርጉም መጠቀም ለዚህ የስልጠና አነስተኛ መጽሐፍ የተሻለ ነው።

# ትምህርት 1
# መንፈሳዊ ቤተሰብ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው፡፡

1. ኢየሱስ ስለ እኛ ምን አለ? ማቴ 23:8

2. ኢየሱስ የአንተ መንፈሳዊ አባት ማን ነው አለ? ማቴ 23:9

3. ኢየሱስ የእሱ ቤተሰብ አባል እንሆን ዘንድ ከልባችን ምን እንድንፈልግ ነገረን? ማቴ 12:50

4. ሌላው ቤተክርስቲያንን የሚገልጽ ቃል ምንድ ነው? ሮሜ 12:5

5. የአካሉ ራስ ማን ነው? ቆላ 1:18

6. የክርስቶስ አካል ክፍል እንዴት እንሆናለን? ገላ 3:27-28, 1 ቆሮ 12:13

7. ሌላው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን የሚመለከትበት መንገድ ምንድ ነው? 1 ቆሮ 3:9, ዕብ 3:6, 1 ጴጥ 2:5 & 9

8. ቤተክርስቲያንን የሚያንጸው ማን ነው? ዕብ 3:4

9. በመጨረሻ የቤተክርስቲያን እጣ ፈንታ ምን ይሆናል? 2 ቆሮ 11:2, ራዕ 19:7-8

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በፍጹም ልብህ በመሻት ራስህን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አድርገህ ትመለከታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን እግዚአብሔር ፈቃዱን ትፈጽም ዘንድ በፍጹም ልብህ መሻት እንዲሰጥህ ጸልይ፡፡

2. የውኃ ጥምቀት ወስደሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, የቤተክርስቲያንህ መጋቢ እንዲያጠምቅህ ጠይቅ፡፡



3. የቤተክርስቲያን ራስ ከሆነው ኢየሱስ ወይም ከእግዚአብሔር አብ ይልቅ ዓይንህን በሌላ ሰው ላይ ጥለሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ, አሁን ንስሀ ግባ የቤተክርስቲያን ራስ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማክበር ጀምር።

**ማስታወሻ:** **ማቴ** 12፤50 የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ቤተሰብ መሆኗን በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

# ትምህርት 2

# የመንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. የቤተክርስቲያን ራስ እና አባት ማን ነው? ማቴ 23:9, ቆላ 1:18

2. ለአባትነት ያልተጠራን ቢሆንም እንኳን አባት ልንሆን የምንችልበት መንገድ ምንድ ነው? 1 ቆሮ 4:15

3. ለኢየሱስ እንዴት መኖር እንዳለብን ያስተማሩን የቀድሞ ወንድሞች እና እህቶች እነማን ናቸው? ኤፌ 4:11-15

4. ሌሎች አባላት እነማን ናቸው ምንስ እንዲሰሩ ተጠሩ? ሮሜ 12:6-8, 1 ቆሮ 12:28

5. አንድ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚኖረውን ስፍራ የሚወስነው ማን ነው? 1 ቆሮ 12:18, 2 ጢሞ 1:9

6. እግዚአብሔር የሰጠንን ጥሪ በህይወታችን እናገኝ እና እንፈጽም ዘንድ የሚረዱን ሁለት ነገሮች ምንድ ናቸው? ሮሜ 12:6, 2 ጢሞ 1:9

7. የተሰጠንን የጸጋ ስጦታዎች እና ጥሪዎች ለማረጋገጥ ታላላቅ ወንድሞቻችን የሚያበረክቱት ድርሻ ምንድ ነው? 1 ጢሞ 4:14, 2 ቆሮ 13:1

8. እግዚአብሔር የመንጋው (የመንፈሳዊ ቤተሰብ) እረኛ (መሪ) እንዲሆን የጠራው ማንን ነው? 1 ጴጥ 5:1-3

9. የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ለመሆን መስፈርቶቹ ምንድ ናቸው? 1 ጢሞ 3:1-7, ቲቶ 1:5-9

10. አንድ ሰው እንዴት ሽማግሌ ሊሆን ይችላል? ቲቶ 1:5, ሐዋ 14:23

11. የቤተክርስቲያን ምዕመናን የሚያስፈልጋቸውን ከማገልገል አንጻር ቤተክርስቲያንን ያገለግል ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠው ማንን ነው? ሐዋ 6:1-3, ፊሊ 1:1

12. ዲያቆን ለመሆን መስፈርቶቹ ምንድ ናቸው? 1 ጢሞ 3:8-13

13. አንድ ሰው እንዴት ዲያቆን ሊሆን ይችላል? ሐዋ 6:1-3

14. ቤተክርስቲያንን ይመሩ ዘንድ በእግዚአብሔር የተሾሙትን እንዴት ነው የምንከተላቸው? ዕብ 13:7 እና 17

***መሠረታዊ ጥያቄዎች*:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. በቤተክርስቲያን (መንፈሳዊ ቤተሰብ) ውስጥ ያለህን ስፍራ ለማወቅ እግዚአብሔርን ፈልገህ ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን ፊቱን ፈልግ።

2. በህይወትህ የእግዚአብሔርን አላማ በህይወትህ ለመፈጸም በእግዚአብሔር ጸጋ (በማይገለጥ አቅምና ጥበብ) ትደገፋለህን ወይስ በራህ አቅምና ችሎታ? በእግዚአብሔር ጸጋ __ በራሴ ችሎታ __ በራስህ አቅምና ችሎታ የምትታመን ከሆነ ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔርንም የሱን ፈቃድ ትፈጽም ዘንድ በሱ ጸጋ መደገፍ እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

3. በአንተ መንፈሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ለእግዚአብሔር መሪነት ትገዛለህን፤ለአገልግሎት እንዲያስተምሩህም ትፈቅዳለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር የሚታዘዝ ልብ እንዲሰጥህ ጸልይ።

4. የክርስቶስ ቤተሰብ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን የምትመራ መንፈሳዊ አባት ነህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, ንስሀ ግባ፤ጌታ ኢየሱስ ይህንን ማድረግ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

**ማስታወሻ:** **1ኛ ቆሮ 12፤8** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።




*ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የሚሰራው ሥራ አለው*

# ትምህርት 3
# መንፈሳዊ ቤተሰብ መሆን

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ከወንድሞቻችን እና ከእህቶቻችን ጋር የሚኖረን ህብረት ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረን ህብረት ምን ይነግረናል? 1 ዮሐ 4:20-21

2. ድሀ እና ሀብታም እርስ በእርሳቸው እንደ የክርስቶስ አካልነታቸው እንዴት መዋሃድ ይችላሉ? ያዕ1:9-10, 2:1-9; ሮሜ 12:16; 1 ጢሞ 6:17-19

3. አንድ ወጣት ከአንድ በእድሜ ከገፋ የክርስቶስ አካል እና በተመሳሳይ እድሜ ላይ ካለ ሰው ጋር እንዴት መዋሃድ ይችላል? 1 ጴጥ 5:5, 1 ጢሞ 5:1-2

4. ጠንካራ የሆነው የክርስቶስ አካል ደካማ ለሆኑት ያለባቸው ኃላፊነት ምንድ ነው? ሮሜ 14:1-5, 21, 15:1; 1 ቆሮ 8:7-13, 9:22; 1 ተሰ 5:14

5. የአካሉን ተከታይ አባላት አገልግሎትን በተመለከተ የእኛ ኃላፊነት ምንድ ነው? 2 ቆሮ 8:12-15, 9:6-13; ያዕ 2:15-16; 1ዮሐ 3:17; ገላ 6:7-10

6. ህብረትን ለማፍረስ ያሉን ምክንያቶች ምንድ ናቸው? ሮሜ 16:17, 1 ቆሮ 5:4-13, 2 ተሰ 3:11-14, 2 ጢሞ 3:1-5, 2 ዮሐ 7-11

7. ከአካሉ ክፍሎች የተሰበረውን ግንኙነት ለማደስ እንዴት እንፈልጋለን? ገላ 6:l-2, ማቴ 7:1-5, 18:15-20; ያዕ 5:16-20; 2 ተሰ 3:15

8. ከወንድሞቻችን እና ከእህቶቻችን ጋር የሚኖረን ህብረት ለዓለም ምን ይናገራል? ዮሐ 13:35

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ከወንድሞቻችን እና ከእህቶቻችን ጋር የሚኖራችሁ ህብረት ለእግዚአብሔር ስላላችሁ ፍቅር ምን ይናገራል?

2. ለሀብታም የቤተክርስቲያን አባላት የምትሰጡትን ክብር ለድሆችም በተመሳሳይ መንገድም ትሰጣላችሁን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን ንስሀ ግባ፤ ሁሉንም ወንድሞች እና እህቶች በእኩል መውደድ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

3. በእድሜ የገፉ ወገኖችን እንደ ቤተሰብ ትመለከታለህን፤እንዲሁም በተመሳሳይ እድሜ ላይ ያሉትን እንደ ወንድሞች እና እህቶች ትመለከታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን ንስሀ ግባ፤ለሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት ክብር ማሳየት ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

4. በእምነታቸው እንደ አንተ ጠንካራ ያልሆኑ ሰዎችን ዝቅ አድርገህ ትመለከታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር እንደወደዳቸው አንተም ትወዳቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ።

5. በቻልከው መጠን የሌሎችን የቤተክርስቲያን አባላት ቁሳዊ ፍላጎት ይሟላ ዘንድ ለማገልገል ትሻለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር የሌሎችን የቤተክርስቲያን አባላት ቁሳዊ ፍላጎት እንዲሟላ ማገልገል ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

6. ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች ውጪ ከሌሎች ወንድሞች እና እህቶች የተሰበረ ግንኙነት አለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን ንስሀ ግባ፤ግንኙነትን ለማደስ ፈልግ።

7. እንደ እግዚአብሔር ቃል ችግር ካለብህ ወንድሞች እና እህቶች ያለህን የተሰበረ ግንኙነት ለማደስ የቻልከውን ያህል ጥረት አድርገሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን ንስሀ ግባ፤ችግር ካለብህ ወንድሞች እና እህቶች ያለህን የተሰበረ ግንኙነት ለማደስ የቻልከውን ያህል ጥረት አድርግ።

8. የሌላ ቤተክርስቲያን አባላትን የምትቀበሉባቸው መንገዶች ለዓለም ተምሳሌት ሊሆን በሚችል መንገድ ነውን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ የሌላ ቤተክርስቲያን አባላትን መቀበል እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

**ማስታወሻ:** **1ኛ ጢሞ 5፤1-2** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።



*ሁሉንም የእግዚአብሔር ቤተሰብ በፍቅር እና በአክብሮት መቀበል አለብን*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው፡፡

1. ከሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት ጋር ህብረትን መፍጠርን በተመለከተ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ምንድ ነው? ዕብ 10:24-25

2. ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ለህብረት ምን ያህል ጊዜ ይገናኙ ነበር? ሐዋ 2:42, 46-47

3. በህብረት በምንሰበሰብበት ጊዜ የቤተክርስቲያን አካል ሊሆኑ የሚገባቸው አስር ነገሮች ምንድ ናቸው? 1 ቆሮ 14:26, 16:1-2; ሐዋ 2:42

| | |
|---|---|
| ሀ. | ለ. |
| ሐ. | መ. |
| ሠ. | ረ. |
| ሰ. | ሸ. |
| ቀ | በ. |

4. በህይወታችን አንድ ግዜ ብቻ የሚከሰቱ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በህብረት ውስጥ ሊሆኑ የሚገባቸው ሦስት ነገሮች ምንድ ናቸው? ራዕይ 19:7,9; ዕብ 13:4; ሐዋ 2:41; ማር 10:13-16

5. በምን አይነት ደንብ ነው እነዚህ መሆን የሚገባቸው? 1 ቆሮ 14:40

6. በህብረት በምንሰበሰብበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚያደርገው ምንድ ነው? ማቴ 18:20

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. በተቻለህ መጠን የበዛ ጊዜህን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በህብረት ታሳልፋለህን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ,ጊዜህን ከክርስቲያን ወገኖች ጋር በማሳለፍ ህብረት ማድረግ ትችል ዘንድ ህይወትህን ማዘጋጀት እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

2. በህብረት ስንሰበሰብ እግዚአብሔር እናደርግ ዘንድ ያዘዘንን እናደርጋለን?
   አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ከወንድሞች እና ከእህቶች ጋር በህብረት ስትሰበሰቡ እግዚአብሔር ታደርጉ ዘንድ ያዘዛችሁን ማድረግ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ጸልዩ፡፡

3. በህብረት በምትሰበሰቡ ጊዜ እግዚአብሔር ያላዘዘንን ታደርጋላችሁን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ ከሆነ፤አሁን ንስሀ ግባ እግዚአብሔርም እነዚህን ነገሮች ከህይወትህ እንዲያስወግድ ጸልይ።

4. የህብረት ጊዜያችሁ ስርዓት ያለውና እግዚአብሔር ሌሎችን ይባርክ ዘንድ የሚያስችለው ነውን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔርም እነዚህን ነገሮች በአግባቡ እና በስርዓቱ ማከናወን ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

**ማስታወሻ:** **ማቴ 18፤20** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።




*ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር እግዚአብሔርን ለማገልገል እንበረታታ ዘንድ ጊዜያችንን በአንድነት ማሳለፍ አለብን*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# ሀ
# ምስጋና እና አምልኮ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ወደ እግዚአብሔር ህልውና እንዴት እንመጣለን? *መዝ* 100:2,4

2. የእግዚአብሔር ማደሪያ ምንድ ነው? *መዝ* 22:3

3. ምስጋና እና አምልኮ ለእግዚአብሔር ምን ይጠቅማል? *መዝ* 63:3-4

4. ምስጋና እና አምልኮ የሚያመልከውን ሰው በምን መልኩ ይረዳዋል? ኤፌ 5:18-19

5. እግዚአብሔርን ስናመልክ የልብ ሀሳብ እና ፈቃድ ምን መሆን አለበት? ዮሐ 4:23-24

6. ምስጋና እና አምልኮን በተመለከተ ልናደርግ የሚገባቸው ነገሮች ምንድ ናቸው?
   *መዝ* 63:3-4; 95:6; 96:1; 149:1, 3, 5, 6; 150, 29:1-2

7. እግዚአብሔርን ስናመልክ በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ምን ይሆናል?
   2 ዜና 20:14-24, *መዝ* 149:6-9

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. በምስጋና እና አምልኮ ወደ እግዚአብሔር ህልውና መግባት ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ።

2. እግዚአብሔርን የምታመልክባቸው ጥቂት መንገዶች ምንድ ናቸው?

3. እግዚአብሔርን ማምለክ ለመጀመር አዲስ መንገዶች ምንድ ናቸው?

2. 4. በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተህ ትውል ዘንድ የእግዚአብሔርን ህልውና በየቀኑ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ።

5. በምስጋና እና አምልኮ ህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙህን ችግሮች ትፈታ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ህልውናውን ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን አድርገው።

**ማስታወሻ:** <u>መዝ 100፤4</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

*አምልኮ እና ምስጋና ወደ እግዚአብሔር ህልውና ያመጡናል*



# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# ለ
# ጸሎት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. እግዚአብሔር ምን ሰጠን? መዝ 115:16

2. ይህንን ኃላፊነት እንሸከም ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠን ምንድ ነው? ማቴ 18:18-19

3. የእግዚአብሔርን ስራ በአግባቡ ለማከናወን እንችል ዘንድ አቅማችን ለማሳደግ በጸሎት እንዴት እንስማማለን? ዘለ 26:7-9

4. ቅድሚያ የምንሰጠው መንፈሳዊ ነገር ምንድ ነው? 1ጢሞ 2:1-4

5. እንዴት መጸለይ ይኖርብናል? ማቴ 6:9-13

6. ሁኔታዎች ሲያስቸግሩን ምን ማድረግ አለብን? ሉቃ 18:1

7. እርስ በእርሳችን መጸለይ ያለብን ለምን ያህል ጊዜ ነው? ኤፌ 6:18



***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ዓለም ወደ ኢየሱስ እንዲመጣ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ።

2. የእግዚአብሔርን ስራ በአግባቡ ለማከናወን እንድትችል እንዲሁም ኃይል እና መስማማት ይኖርህ ዘንድ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በህብረት ትጸልያለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ጀምር።

3. በጌታ ጸሎት ውስጥ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ትጸልያለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ምሳሌዎቹን አጥናቸው፤በጸሎት ህይወትህም መጠቀም ጀምር።

4. ከሌሎች ጋር መጸለይ እግዚአብሔር በችግር ጊዜ ችግሮቻችንን ለመፍታት የሰጠን አንዱ መሳሪያ እንደሆነ ታምናለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያራልህ ጸልይ።

5. ከሌሎች ክርስቲያን ወገኖች ጋር በመሆን ለቤተክርስቲያን አባላት፤የጠፉ ወገኖች እና ጎረቤታችሁ በመደበኛ ሁኔታ ትጸልያላችሁን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዝርዝር አውጣ እና ዛሬ ማድረግ ጀምር።

6. አንተ ያለህበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በቀን የ24 ሰዓት፤በሳምንት 7 ቀን የሚጸልይ የጸሎት ቡድን አላትን ወይም ትሳተፋለችን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን አንዱን ቀን ለመጀመር ተዘጋጅ።

**ማስታወሻ:** **ማቴ 18፤18-19** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።



*በህብረት ስንጸልይ የበለጠ ኃይል ይኖረናል*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# ሐ
# ትምህርት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. ኢየሱስ በመጨረሻ የሰጠው ትእዛዝ ምንድ ነበር? ማቴ 28:19-20

2. ለመማር ምን ያስፈልገናል? ቲቶ 3:14, ቆላ 1:28

3. የእግዚአብሔርን ነገሮች ስንማር የሚረዳን ማን ነው? ዮሐ 16:13

4. እግዚአብሔር ለሚያስተምረን ነገሮች የእኛ መልስ ምን መሆን አለበት? ቆላ 3:16, ፊሊ 2:12-13

5. እግዚአብሔር እንዲያስተምረን ስንፈቅድ ምን ይሆናል? ምሳ 9:9

6. የእግዚአብሔር ቃል በተገቢው መንገድ ስንማር በክርስቶስ አካል ላይ ምን ይሆናል? ኤፌ 4:11-16

7. እግዚአብሔር ባስተማን ነገሮች ምን ማድረግ አለብን? 2 ጢሞ 2:2

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ለሌሎች ለኢየሱስ እንዲኖሩ በማስተማር እግዚአብሔር እንዲጠቀምብህ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር ሌሎችን ማስተማር ትችል ዘንድ ይህንን መሻት እንዲሰጥህ እና እንዲቀባህ ጸልይ።

2. የእግዚአብሔር ቃል በባለጠግነት እንዲኖር እና በህይወትህ በመታዘዝ እንዲጎለብት ትፈቅዳለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ንስሀ ግባ ይህንን ታደርግ ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

3. ቃሉን በተማርከው መሰረት እግዚአብሔር በህይወትህ ባለው እቅዱ እና ዓላማው እንዲመራህ ትፈቅዳለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያሳይህ ጸልይ።

**ማስታወሻ:** **<u>ቲቶ 3፤14</u>** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።




*እግዚአብሔርን እንዴት ማገልገል እንዳለብን ለማወቅ መማር አለብን*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# መ እና ሠ
# በልሳን መናገር እና መተርጎም

***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤*** *ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው፡፡*

1. በጉባኤ ውስጥ በልሳን መናገር ለምን ይጠቅማል? 1 ቆሮ 14:22

2. በጴንጤ ቆስጤ ቀን በልሳን ሲናገሩ ምን ሆነ? ሐዋ 2:4-41

3. አንድ ሰው በልሳን ሲናገር ሊያስተላልፈው የሚገባው መልዕክት ምንድ ነው? 1 ቆሮ 14:13

4. አንድ ሰው ሲተረጉም እኛ ምን ማድረግ አለብን? 1 ቆሮ 14:28

5. በልሳን መናገር እና መተርጎም ምን ያህል ይጠቅማሉ? 1 ቆሮ 14:27

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** *በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡*

1. የማያምኑ ሰዎችን ታገለግል ዘንድ በልሳን የመናገር ስጦታን ሰጥቶሀልን? አዎ __ አይደለም __

2. ልሳኖችን የመተርጎም ስጦታ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ ጸልየኽ ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ራስህን ለእግዚአብሔር አገልግሎት እያስገዛህ ጸልይ፡፡

3. በልሳን የመናገር የጸጋ ስጦታዎች በስፋት በቤተክርስተያንዎ ውስጥ ይነገራሉን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ፤አሁን በአግባቡ እና በስርዓት መጠቀም ትችሉ ዘንድ ጸልዩ፡፡

4. ተርጓሚ ከሌለ ዝም ትላለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ከአሁን ጀምር፡፡




**ማስታወሻ:** **1ቆሮ 14፤22** *በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡ልሳን እና ልሳንን መተርጎም ለማያምኑ ሰዎች ምስክር ነው*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# ፈ
# ራዕይ

***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤*** *ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።*

1. በጣም ልትሻው የሚገባ መንፈሳዊ ስጦታ ምንድ ነው? 1 ቆሮ 14:1

2. እውነተኛ ትንቢት ለሌሎች ምን ይሰራል? 1 ቆሮ 14:3

3. እውነተኛ ትንቢት ከየት ይመጣል? 2 ጴጥ 1:21

4. እውነተኛ ትንቢት ምን ያመለክታል? ራዕ 19:10

5. የሐሰተኛ ትንቢት ውጤት ምንድ ነው? 2 ጴጥ 2:1-3, 18-19

6. በቤተክርስቲያን ውስጥ የምናገኘው ሌላ አይነት ራዕይ ምንድ ነው? 1 ቆሮ 12:8

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** *በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።*

1. የትንቢትን ስጦታ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር ትንቢት የመፈለግ መሻት እንዲሰጥህ እና ሌሎችን እንድታገለግል ጸልይ።

2. ትንቢት እውነት ወይም ሐሰት መሆኑን ትመረምራለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ጀምር።

3. የጥበብ እና የእውቀት ቃል በህይወትህ እንዲሰራ ትፈቅዳለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ጀምር።

**ማስታወሻ:** 1ቆሮ 14፤1በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

ትንቢት ያበረታናል፤ያፅናናናል፤በጌታ እናድግ ዘንድ ይረዳናል



# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# ሰ
# የጌታ እራት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።

1. የጌታ እራትን ማን ሰጠን ለምንስ ተሰጠን? 1 ቆሮ 11:23-26

2. የጌታ እራን ከመውሰዳችን በፊት ምን ማድረግ አለብን? 1 ቆሮ 11:27-31

3. ለጌታ እራት ስንቀርብ ኢየሱስ ያሳየን ምንድ ነው? ዮሐ 13:1-17

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ሁልጊዜ የጌታን እራት ስትውስድ ጌታ ያደረገልህን ነገር ታስባህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ሁልጊዜ ማድረግን ጀምር።

2. የጌታን እራትን ከመውሰድህ በፊት ልብህን ትመረምራለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ጀምር።

3. እርስ በእርስ እግር መተጣጠብ የጌታ እራትን የመውሰድ ዝግጅት እና የእርስ በእርስ የአገልጋይነት ምልክት እንደሆነ አግኝተዋልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ጀምር።

**ማስታወሻ:** 1ቆሮ 11፤26 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።



*የጌታ እራት ኢየሱስ ለእኛ ያደረገውን ያስታውሰናል*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# ሸ
# የምስጋና ጊዜ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው፡፡

1. የደስታ ጊዜ (የምስጋና ጊዜ) ምንድ ነው? ዘሑ 23:2

2. ለደስታ(ለምስጋና) በምንሰበሰብበት ጊዜ አስተሳሰባችን ምን መሆን አለበት? 1 ቆሮ 5:8

3. በምንሰበሰብበት ጊዜ እውነተኛ ህብረት ለመፍጠር ከእኛ ምን ይጠበቃል? 1 ዮሐ 1:1-3, 6-7

4. ከሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት በተጨማሪ ለደስታ(ምስጋና) ጊዜ መጋበዝ ያለብን እነማንን ነው? ሉቃ 14:13-14

***መሠረታዊ ጥያቄዎች*:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. የእግዚአብሔርን ሥራ ለማክበር የተለየ ጊዜ ታዘጋጃላችሁን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ማድረግ ጀምር፡፡የተለየ ጊዜያት ለምሳሌ የገና በዓል፤የትንሳኤ በዓል እና ልዩ ባዕላት የእግዚአብሔርን ሥራ ለማክበር ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡

2. እግዚአብሔር የሰራውን ሥራ ምክንያት በማድረግ እሱን የደስታህ ጊዜ ማዕከል ታደርጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እሱን የደስታህ ጊዜ ማዕከል ማድረግን ጀምር፡፡

3. በምትጾምበት ጊዜ ችግረኞችን ትጋብዛለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር ይህንን ማድረግ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

**ማስታወሻ:** <u>**1ዮሐ 1፤7**</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡




*የምናዘጋጀው የደስታ ጊዜ ኢየሱስ ለእኛ ያደረገውን ሊያስታውሰን ይገባል*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# ቀ
# መስጠት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው፡፡

1. ትልቁን ስጦታ የሰጠን ማን ነው? ዮሐ 3:16

2. እግዚአብሔር በስጦታው ምን ይሰጠናል? ሮሜ 8:32

3. እግዚአብሔር ይባርከን ዘንድ ምን እንድናደርግ ይጠይቀናል? ሚልኪያስ 3:10

4. ይህ የእውነት የኢየሱስ ክርስቶስ የምስራች ወንጌል ይሰበክ ዘንድ ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን የምትሰጠው ምንድ ነበር? ሐዋ 2:44-45; 4:32

5. ኢየሱስ አስራት እና መባን በተመለከተ ምን አለ? ማቴ 23:23

6. ለእግዚአብሔር መጀመሪያ መስጠት ያለብን ምንድ ነው? 2 ቆሮ 8:5

7. ስንሰጥ የልባችን አመለካከት ምን መሆን አለበት? 2 ቆሮ 9:7

8. ስንሰጥ ልንመራ የሚገባ በምንድ ነው? 2 ቆሮ 8:12-15

9. ይህ እኛ በምንሰራበት መንገድ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል? ኤፌ 4:28

10. በመስጠታችን እግዚአብሔር የሚሰራው ምንድ ነው? 2 ቆሮ 8:13-15

11. አስራታችንን መስጠት ያለብን ለማን ነው? ገላ 6:6, 1ጢሞ 5:17-18

12. ለሰዎች መባን መስጠት ያለብን መች ነው? ገላ 6:10, ምሳ 3:27-28

13. ለእግዚአብሔር ስራ አስራታችንን እና መባችንን መስጠት አለብን? 1 ቆሮ 16:2

14. መስጠትን በተመለከተ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ምንድ ነው፡፡መክብብ 11:1, 2 ቆሮ 9:6

15. በታማኝነት መስጠት ለእኛ ምን ይሰጠናል? 2ቆሮ 9:8

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. በቁሳዊ ነገር ያገኘሽው በረከት ከእግዚአብሔር እንደሆነ ታምናለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያበራልህ ጸልይ፡፡

2. ሙሉ ለሙሉ ለመባረክ ለእግዚአብሔር መስጠት እንዳለብህ ታምናለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር ይህንን እውነት እንዲያራልህ ጸልይ፡፡

3. ለሚያንገሁ ነገሮች ገንዘብ ከመስጠጥ ይልቅ የክርስቶስ ኢየሱስን የምስራች ወንጌል ይሰበክ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ውስጥ ሆነህ ለመታዘዝ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን የእግዚአብሔርን ጥበብ እና ምሪት መፈለግን ጀምር፡፡

4. ከገቢህ አስር እጅ የሚሆነውን ለሚመሩህና ለሚያስተምሩህ የወንጌልን ስራ በሚገባ ይሰሩ ዘንድ ትሰጣለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር፡፡

5. መባን የወንጌል ስራ ይሰራ ዘንድ እና ለሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ከአስራትህ አስበልጠህ ትሰጣለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር፡፡

6. በመስጠት ህይወት ውስጥ ለመኖር በጣም ደስተኛ የሆነ አመለካከት አለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ እግዚአብሔር ደስተኛ እና በፈቃዱ የሚሰጥ ሰው እንዲያደርግህ ጸልይ፡፡

**ማስታወሻ:** <u>**ሚልኪያስ** 3፤10</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡



*ሁሉም የእግዚአብሔር ቤተሰብ ይባረክ ዘንድ የተቻለንን ያህል መስጠት አለብን*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል 1
# ህብረት
# በ
# አገልግሎት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው፡፡

1. ሊገለገሉ የሚገባቸው የሰው ሦስት አካል ምንድ ናቸው? 1 ተሰ 5:23

2. በአገልግሎታችን ቅድሚያ የሚሰጠው ማን ነው? ገላ 6:10

3. ሰዎችን በሚገባ እናገለግል ዘንድ እንዴት መመልከት ያስፈልገናል?
2 ቆሮ 5:16, 1 ቆሮ 2:13-16

4. ሌሎችን ስናገለግል የልባችን አመለካከት ምን መሆን አለበት? 1 ቆሮ 8:1; 16:14

5. መንፈስ እና ነፍስን ለማገለግል የእግዚአብሔር ኃይል ምንድ ነው?
ዕብ 4:12

6. ነፍስና መንፈስን በእግዚአብሔር ቃል እንዴት እናገለግላለን? 2 ጢሞ 3:16; 4:2

7. ቃሉን እናገለግል ዘንድ እንዲረዳን መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን መንፈሳዊ ስጦታዎች ምንድ ናቸው?
1 ቆሮ 12:8 & 10

8. ነፍስና መንፈስን ከማገልገል ሌላ የምናገለግለው ምንድ ነው?
ያዕ 2:15-16, 5:14-15; 1 ቆሮ 12:9

9. ሌሎችን ማገልገልን በተመለከተ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ምንድ ነው? ምሳ 3:27-28

10. ሌሎችን ስናገለግል ሁልጊዜ ለማድረግ መፈለግ ያለብን ምንድ ነው?
ማቴ 5:16; 1 ቆሮ 4:12, 10:31-32

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ሌሎችን ስታገለግል፤ሰውን ሁለንተውን ልታገለግል ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ ዛሬ ማድረግ ጀምር።

2. ሌሎችን ከማገልገልህ በፊት መንፈሳዊ ቤተሰብህን ልታገለግል ትሞክራለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤መጀመሪያ ቅዱሳንን በማገልገል ጀምር።

3. ሌሎችን የምታገለግለው በመንፈሳዊ ዓይን በመመልከት ነው ወይስ በስጋዊ ዓይን? በስጋዊ ዓይን ከሆነ ንስሀ ግባ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ዓይን እየተመለከትክ ማገልገል እንድትችል እንዲረዳህ ጸልይ።

4. የእግዚአብሔርን ቃል በማንኛውም መንገድ እግዚአብሔር ታገለግላቸው ዘንድ ወደ ላከህ ነፍስና መንፈስን ለማገልገል ትጠቀምበታለህን? አዎ __ አይደለም __ዛሬ ማድረግ ጀምር።

5. የምታገለግለው ከፍቅር እና ልባዊ መሻት ተነስተህ ነው ወይስ ሐይማኖታዊ ተግባርን ለማሟላት እና ለራስ ክብር ነውን? ሐይማኖታዊ ተግባርን ለማሟላት እና ለራስ ክብር ከሆነ ንስሀ ግባ፤አሁን እግዚአብሔር በፍቅር እንድታገለግል መልካም ልብ እንዲሰጥህ ጸልይ።

6. ወገኖችን በተቻልከው ፍጥነት ታገለግላህ ወይስ አገልግሎትህን በአግባቡ አትወጣም? አገልግሎትህን በአግባቡ የማትወጣ ከሆነ ንስሀ ግባ፤በአገልግሎትህ እግዚአብሔር ስነ ስርዓትን እንዲሰጥህ ፀልይ።

7. ሌሎችን ለማነጽ እና እግዚአብሔርን በማክበር ለማገልገል ትሻለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ እግዚአብሔር የአገልግሎት ልብ እንዲሰጥ ጸልይ።




**ማስታወሻ:** ማቴ 5፤16 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።



*የሠዎችን አዕምሮአዊ፤ስሜታዊ፤አካላዊ እና ቁሳዊ ፍላጎት ማገልገል አለብን*

# ትምህርት 4
# የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህይወት
# ክፍል2
# ወንጌል መስበክ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤***ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።*

1. ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሠጠው የመጨረሻው ቃል ምን ነበር? ማቴ 28:18-20

2. የሱን ወደ ዓለም ሁሉ ሄዶ የመስራች ወንጌልን ስለ መስበክ ትዕዛዝ ምን አለ? ሐዋ 1:8

3. ለሌሎች ስለ ኢየሱስ እንድንናገር ኃይልን እናገኝ ዘንድ በየዕለቱ ማድረግ የሚገባን ምንድ ነው? ሐዋ 4:31

4. ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ለመናገር መጸለይ ያለብን ምን አይነት ጸሎት ነው? 1 ጢሞ 2:1-4, ሉቃ 18:1

5. ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ለመናገር በቃሉ ምን ማድግ አለብን? 1 ዮሐ 1:1-3

6. ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ስንናገር አመለካከታችን ምን መሆን አለበት?
   መዝ 126:5-6, 2 ጢሞ 2:24-26

7. ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች ሰዎች ሲያስተምር ምን አደረገ? ዮሐ 4:5-26

8. መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን የሚወቅስበት ሦስት ነገሮች ምንድ ናቸው? ዮሐ 16:7-11

9. ምን ማካፈል አለብን፣የት ማካፈል አለብን፣እንደ ሐዋ 20:21, & ሉቃ 8:5-8, 11-15 ገለጻ ውጤቱን የሚወስነው ምንድ ነው?

10. ቃሉን ከመስበክ ሌላ ልናደርግ የሚገባን ምንድ ነው? ማቴ 10:7-8

11. ኢየሱስን ለሌሎች ስንሰብክ ልንጠቀም የሚገባን ሁለት አቀራረቦች ምንድ ናቸው? ይሁዳ 22-23

12. እንደ ሮሜ 3:23, 6:23, 5:8, 2:4, 10:9-10, & 6:17-18 ገለጻ ስለ ኢየሱስ የሚናገረው መልዕክት ምንድ ነው ?

13. ኢየሱስን ለሌሎች ስንሰብክ ልናስወግድ የሚገቡን ሁለት ነገሮች ምንድ ናቸው? ቲቶ 3:4-9, 2 ቆሮ 4:1-6

14. ኢየሱስን ለሌሎች ስንሰብክ ማድረግ የሌለብን ምንድ ነው? ገላ 6:9

15. ኢየሱስን ለሌሎች ስንሰብክ እግዚአብሔር የሰጠን የተስፋ ቃል ምንድ ነው? ኢሳ 55:10-11

16. ኢየሱስ ቃሉን ይሰብኩ ዘንድ ሰዎችን እንዴት ላካቸው? ሉቃ 10:1-2

17. ጥንታቷ ቤተክርስቲያን ስለ ኢየሱስ እንዴት ሰበከች? ሐዋ 2:32, 4:31, 8:4

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ትናገራለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፣በማንኛውም አጋጣሚ ስለ ኢየሱስ መናገርን ጀምር፡፡

2. በአከባቢህ የሚደረግ የወንጌል ስብከት የቤተክርስቲያን አንዱ የወንጌል ስብከት አካል ነውን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፣የአጥቢያ ቤተክርስቲያንህ አመራር የአገልግሎቱ አካል ማድረግ ይችል ዘንድ ጸልይ፡፡

3. የአጥቢያ ቤተክስቲያንህ በዓለም ዙሪያ ለሚደረግ የወንጌል ስብከት ሰዎችን እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በዓለም ዙሪያ በመላክ ይሳተፋልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፣ከሆነ፣የአጥቢያ ቤተክርስቲያንህ አመራር የአገልግሎቱ አካል ማድረግ ይችል ዘንድ ጸልይ፡፡

4. የአጥቢያ ቤተክስቲያንህ የምታስተላፊው የወንጌል ስብከት መልዕክት በሮሜ ውስጥ በአንዱ ከተጠቀሳው ላይ ያተኩራልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፣አሁን ቤተክስቲያንህን በእነዚህ ነጥቦች ላይ ማተኮር እንድትችል ጸልይ ባገኘኸውም አጋጣሚ አካፍቸላው፡፡

5. የአጥቢያ ቤተክስቲያንህ ህብረት በዓለም ዙሪያ ለሚደረግ የወንጌል ስብከት ትጸልያለችን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ቤተክስቲያንህን ምዕመናን በዓለም ዙሪያ ለሚደረግ የወንጌል ስብከት እና ለሚጸፉ ነፍሳት ይጸልዩ ዘንድ አበረታታ፡፡

6. ውጤት ባታይም እንኳን በወንጌል ስብከትህ ቀጥለሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤በዚህ አከባቢ ታማኝ መሆን ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

**ማስታወሻ**: <u>**ሐዋ 20፤21**</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡



<u>**የእግዚአብሔር ቤተሰብ ስለሆነችው ቤተክርስቲያን የተሰጠውን ተጨማሪ መግለጫ በአግባቡ ማንበብህን እርግጠኛ ሁን**</u> **፡፡ስለምትማረው የተሻለ ማብራሪያ ይሰጡሀል፡፡**

*የምስክረንት ኃይል ይኖረን ዘንድ መጸለይ አለብን*

# *መሠረታዊ*
# የቤተክርስቲያን ህይወት
# ተጨማሪ መግለጫ

# የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆነቸው ቤተክርስቲያን እና በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ህብረት ውስጥ ላለ ህብረት መመሪያ




Figure 2

Figure 1

ቤተክርስቲያን በተለያየ በርካታ መንገድ ስትገለጽ እንሰማለን፡፡በርካታ ሰዎች ቤተክርስቲያን የተወሰኑ አማኞች በአጥቢያ ወይም በኃይማኖት ስርዓት የሚሰበሰቡበት ነው ብለው ይናገራሉ፡፡በርካቶች ደግሞ ቤተክርስቲያን ሰዎች ያለበት ወይም የሌለበት ህንጻ ነው ብለው ያምናሉ፡፡እነዚህ አመለካከቶች በእግዚአብሔር ዘንድ የተለያየ ቤተክርስቲያን አለ የሚለውን ሀሳብ የሚያጎላ ነው፡፡ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳብ ጋር አይስማማም፡፡ቤተክርስቲያን በዓለም ተጽዕኖ ማሳደር እንድትችል የሚያደርጋትን አለመስማማት ወይም በአንድነት አለመስራትን የሚያጎላ ነው፡፡

ቤተክርስቲያን ሰው እንጂ አንድ ስፍራ አይደለም፡፡ ኢየሱስን በእምነት በሚከተሉ አማኖች የተገነባ ቤተሰብ ነው፡፡ማቴዎስ 18 ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ አባላት በኢየሱስ ስም ቢሰበሰቡ ቤተክርስቲያን በስልጣን በዚያ እንደምትሆን ግልጽ አድርጎ ያስቀምጣል፡፡ኢየሱስ በተለየ መንገድ እንደሚገለጥ ይናገራል ምክንያቱም እሱ ህያው ነው፤ቤተክርስቲያን ነገሮች እንዲገለጡ የማድረግ ኃይል አላት፡፡ልታቆማቸውም ወይም በእንቅስቃሴ ላይም እንዲሆኑ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ዕብራውያን 10:24-25 በአንድነት ወደ እሱ ስንጠጋ የበለጠ በህብረት ልናገኝ እንደምንችል ይናገራል፡፡የበለጡ ነገሮች ይሆኑ ዘንድ ልናገኛቸው የሚገቡን በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ዛሬ በርካታ ቤተክርስቲያኖች የወገኖችን ህብረት በህንጻ ቀይረውታል፡፡ ምንጊዜም ኃይል አይኖርም ምክንያቱም እነሱ በኢየሱስ ስም የተሰበሰቡ ቢሆንም እነሱ ግን በእውነት የተሰበሰቡት በአንድ ድርጅት ወይም ጎራ ተከፍለው ነው፡፡የእሱን ቤተሰብ እና በየዕለቱ አብረውን የሚኖሩ ሰዎችን እየገፋን እሁድ የአምልኮ ፕሮግራም በእሱ ስም ብንሰበሰብ ይህ በእውነት ክርስቶስን ያሳዝናል፡፡እርስ በእሳችን እየተዋደድን ለማያምነው ህዝብ የእሱን ፍቅር ማሳየት አለመቻል ዓለም ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይመለከት ያደርጋል፡፡እሱ እንሆን ዘንድ እንደሚፈልገን ቤተክርስቲያን ለዓለም ጨው እና ብርሀን ትሆን ዘንድ ያዳግታታል፡፡

ሁለት ሆነን በአንድነት በስሙ ስንሰበሰብ እሱ በምድር ሊሰራ የሚፈልገውን ይሰራ ዘንድ እሱ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳለ ማሰብ አለብን፡፡ለእሱ እውቅና ስንሰጥ እና ለዓላማው ስንኖር እሱ በሰዎች ልብ መንግስቱን ያሰፋ ዘንድ በእኛ ይሰራል፡፡ይህ ይሆን ዘንድ ስንጠይቅ እሱ ማንኛውንም ነገር ያደርጋል፡፡ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ቤተሰብ ህብረት ላይ እንድትሰራ ተመስርታ የተዋቀረች ቡድን እንደነበረች ልንረዳ ይገባል፡፡

ይህ ህይወት እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እንትኖረው የሚፈልገው ነው፡፡ይህ እሱ ቤተክርስቲያንን እንደሚያየው መንገድ ከማየት ይጀምራል፡፡የአማኞችን ቤተሰብና ዓላማውን በእግዚአብሔር ዓይኖች ማየት ይኖርብናል፡፡ዓላማው የእግዚአብሔርን መንግስት በሰዎች ልብ ላይ መመስረት ነው፡፡ ይህ ሁሉንም ሰው በተለይ እግዚአብሔርን ቤተሰብ እንድናገለግል መሪት ይሆነናል፡፡ለሰዎች በመጸለይ፤የሚያነቃቃ ቃል በማካፈል ወይም የሚያስፈልጋቸውን ነገር በማገልገል ጨውን እና ብርሀን የመሆን እድሎችን እንፈልግ ዘንድ ምክንያት ሊሆነን ይገባል፡፡የስራው መጠን በህብረት ከሌሎች ጋር ሆነን እንሰራ ዘንድ ሊያነሳሳን ይገባል፡፡

ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጣውን የኢየሱስን ኃይል ስንመለከት ከሌሎች አማኖች ጋር በህብረት ለመስራት እንቧደናለን፡፡ከአማኞች ጋር እርስ በእርሳችን ፍቅር እና መልካም ስራዎችን ለመግለጽ በመደበኛ ሁኔታ በአንድነት ለመስራት እንሰበሰባለን፡፡የጠፉ ነፍሳትን ለመፈለግ እንቸኩላለን፡፡ሐይማኖት ስርአትን ለሟሟት የእሁድ የአምልኮ ቤተክርስቲያንን ከመካፈል ያለፈ ስራ እንሰራለን፡፡ከአማኞች ጋር እርስ በእርሳችን ቃሉን እየተካፈልን እና እየጸለይን እያንዳንዱን ቀን እናሳልፋለን፡፡በምንሰራበት ስፍራ ከአማኖች፤ከጎረቤቶቻችን ጋር በአንድነት እንሰበሰባለን፤ወይም ወንጌልን ልንሰብክ በምንሔድበት ትምህርት ቤት እንዲሁም ለእያንዳንዳችን እና ለሚያስፈልገን ነገር ለመጸለይ እንበረታለን፡፡መሪ ከሆንን

ከሌሎች መሪዎች ጋር ለህብረት እና ለጸሎት እንሰበሰባለን፡፡ለወንጌል መኖር የህይወታችን አካል ይሆናል፡፡በመሆኑም ኢየሱስ እንደሚፈልገው የሱ ቤተክርስቲያን ጨው እና ብርሀን ትሆናለች፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ ቤተሰብ ህብረትን ለማሳደግ የተጠቀሙት የስልጣን ተዋረድ ስልት ሳይሆን በቡድን የሚመራ የአገልጋይ መሪዎች ህብረት የእግዚአብሔር መንጋ እና የእግዚአብሔር ሥራ ነው፡፡ቤተክርስቲያን እራሷን በሁለት መልክ ገለጻለች፡፡የመጀመሪያው ከአንድ ከተወሰነ ስፍራ የተሰበሰሱ ሁሉም አማኞች የሚሰበሰበት የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ይህ የሚመራው በመጋቢ ሳይሆን በሽማግሌዎች ነው፡፡ይህ እኩል የመንፈሳዊ ብስለት ያላቸው ከሶስት እስከ አስራ ሁለት የሚሆኑ ከእግዚአብሔር ምሪት እና ቃል ይሰሙ ዘንድ እና ቤተክርስቲያንን ለመምራት እና ዓላማውን ለማስፈፀም ራሳቸውን ለቃሉ እና ለጸሎት የሰጡ ሰዎች ናቸው፡፡ ሁለተኛው ሐዋሪያዊ የወንጌል ስብስብ ነው፡፡ይህ ሁለት ተመሳሳይ መንፈሳዊ ብስልት ያላቸውን ሰዎች የያዘ እና በሌላ ቤተክርስቲያን አባላት የተዋቀረ ነው፡፡እነሱ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን የምስራቹን የመዳን ወንጌል ለዓለም ያደርሱ ዘንድ የተላኩ ናቸው፡፡የሚከተለው ግልጽ የሆነ የቤተክርስቲያን መግለጫ ማብራሪያ እና እንዴት በአንድነት እንደሚሰሩ የሚያሳይ ነው፡፡

## <u>የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ህብረት</u>

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሕብረት ቤተሰቢያዊ አንድነት ነው፡፡
እያንዳንዱ ቡድን ከስምንቱ መሰረታዊ የቤተክርስቲያን ህይወት አንዱን የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡አንድ ሽማግሌ እያንዳንዱን ቡድን መከታተል ይኖርበታል፡፡
ከመንፈስ ቅዱስ የሚፈስ ህይወት እያንዳንዱን ቡድን እንዲመራ ሊፈቀድለት ይገባል፡፡

ስምንቱ ቡድኖች፡

1. <u>የጸሎት ቡድን:</u> አጥቢያ ቤተክርስቲያንን የጸሎት አስፈላጊነት ሁልጊዜ በማሳወቅ ያገለግላሉ፡፡እንዲሁም የቤተክርስቲያን የህብረት ጸሎት ፕሮግራም ዝርዝር እና ለአስቸኳይ ጊዜ የጸሎት ህብረት ትስስር ያዘጋጃሉ፡፡ቡድኑ ቤት ለቤት የሚደረግን የጸሎት ፕሮግራም ያበረታታሉ፤እንዲሁም ለቤተክርስቲያን በግል እና በቡድን የጸሎት ጊዜ እንዴት እንደሚዘጋጅ ያስተምራሉ፡፡በተጨማሪም፤የጸሎት ስብሰባን እና በቤተክርስቲያን ምዕመናን የሚደረግ (24-7) የምልጃ ፕሮግራምን ይደረግ ዘንድ(ቢያንስ 2 ወይም 3 ሰዎች በየቀኑ ቀኑን ሙሉ ተሰብስበው ሊጸልዩ ይገባል)በቤተክርስቲያን ውስጥ በመመስረት ሊመሩ ይገባል፡፡

2. <u>የምስጋና እና የአምልኮ ቡድን:</u> አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ወደ እግዚአብሔር ህልውና ትገባ ዘንድ በቡድን በመሰብሰብ አምልኮ በመምራት ይመራሉ፤አዳዳስ መዝሙሮችን ያስተዋውቃሉ፤እንዲሁም ህዝቡን ሙዚቃን እና ምስጋና እና አምልኮንን ያለማምዳሉ፡፡

3. <u>ሰበካ ጉባኤ</u>: አጥቢያ ቤተክርስቲያንን የእግዚአብሔርን ራዕይ እና አስፈላጊ ጉዳዮችን በመደበኛ ስብሰባ በማካፈል ይረዳሉ፡፡

4. <u>ደቀመዝሙር የሚያድርግ(የሚያሰልጥን) ቡድን:</u> ሰዎች ለክርስቶስ ይኖሩ ዘንድ፤የምስራቹን ወንጌል ይሰብኩ ዘንድ እና ሌሎችን ለኢየሱስ እንዲኖሩ ይረዱ ዘንድ በክርስቲያን አገልግሎት እና ኑሮ ስልጠናን ይመራሉ፡፡እንዲሁም ሰዎች እግዚአብሔር የተሰጣቸውን አገልግሎት ያገኙና በሚገባ ይፈጽሙ ዘንድ ያሰለጥኑ ዘንድ ይሻሉ፡፡በተጨማሪም ህጻናት ለጌታ ይኖሩ ዘንድ የሚበረታቱበት፤የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍትን የሚማሩበት እና ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እና ምሳሌዎችን የሚማሩበትን ስፍራ ያዘጋጃሉ እንዲሁም በህይወታቸው እንዴት እንደሚተገብሩ የሚያስተምሩ የህጻናት ቡድን ያዘጋጃሉ፡፡ሌላው ወጣቶች ለጌታ ይኖሩ ዘንድ የሚበረታቱበት፤እና ለኑሯቸው የጌታን ፈቃድ የሚፈልጉበት የወጣቶች ቡድን ያቋቁማሉ፡፡በእነዚህ

ቡድኖች ወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ለመስራት ሊመሩ እና በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ላይ የጋለ ጥናት ሊካሄዱ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት በኑሯቸው፤በጉዳዮቻቸው እና በሚያጋጥማቸው ችግሮቻቸው ላይ ለመተግበር መማር አለባቸው።የደቀመዝሙር ቡድን አዲስ ወደ ጌታ የመጡ እና ቀድሞ አማኝ ሆነው ወደ ቤተክርስቲያን ህብረት የመጡ አዲስ መጪ ታላላቅ ወንድሞች እና እህቶች ግንኙነትን መመስረት እና በሚቻልበት ስፍራ አነስ ያሉ ለስልጠና የተዘጋጁ ቡድኖችን መመምራት መርዳት አለበት።

5. <u>የወንጌል ሰባኪ ቡድን:</u> ለጠፉ ነፍሳት ሸክምን በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያስተምራሉ።በአጥቢያ ውስጥ የሚደረግ ልዩ የሆነ የወንጌል ስርጭት ለምሳሌ የጎዳና እና የክሩሴድ አገልግሎት በማዘጋጀት ያገለግላሉ።የአጥቢያ የወንጌል ስርጭት ቡድንን በማደራጀት ሊረዱ ይገባል።በተጨማሪም የቤት ለቤት ህብረትን በመምራት እንዲሁም የቤተክርስቲያን ምዕመናንን ምስክር ይሆኑ ዘንድ ስልጠና በመስጠት ሊረዱ ይገባቸዋል።

6. <u>የወንጌል ተልዕኮ ቡድን</u>: ቤተክርስቲያን ዓለምን በወንጌል ስለመድረስ ሁልጊዜ ያገለግላሉ፤ሰዎችን ለወንጌል ስራ ይዘጋጁ ዘንድ ያሰለጥናሉ፤<u>ሐዋሪያዊ የወንጌል ተልዕኮ</u> ቡድንን በመላክ ይመራሉ።

7. በአጠቃላይ የቤት ለቤት ህብረት (በቤት ውስጥ የሚደረግ የቤተክርስቲያን ህብረት) የሚከተሉትን ያካትታል፡

<u>መጋቢ/መሪ:</u> የቡድኑ አገልጋይ መሪ ነው።ኃላፊነት የሚሸከም፤ቡድኑን ለመምራት እና ለማበረታታት እና አገልግሎታቸው ማግኘት እና ማከናወን ነው።እሱ መሪ ወይም በአንድ መሪ ምሪት ስር መሆን አለበት።

<u>መጋቢ/ ረዳት መሪ:</u> የቡድኑን ፍላጎት ለማገልገል እና ቡድኑ አገልግሎቱን እንዲያገኝ እና አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙ ለማበረታታት ከዋና መጋቢው ወይም መሪው ጋር አብሮ ለመስራት ኃላፊነትን የሚሸከም ነው።በመንፈሳዊ ብስለት የሚያድግ እና አገልጋይ መሪ ለመሆን የተማረ ነው።

<u>የጸሎት መሪ:</u> የአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ የጸሎት ቡድን የተሰጠውን የጸሎት አገልግሎት ድርሻ በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።

<u>የአምልኮ እና የምስጋና መሪ:</u> ቡድኑን በአምልኮ እና መስጋና ለመምራት ኃላፊነትን የሚሸከም ነው።

<u>የወንጌል ስብከት/የወንጌል ተልዕኮ መሪ:</u> የአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ የወንጌል ስብከት እና ተልዕኮ ቡድን የተሰጠውን የምሥራቹን ወንጌል ለዓለም የማድረስ አገልግሎት ድርሻ በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።

<u>የዲያቆናት መሪ:</u>ቡድኑን ቁሳዊ እና አስፈላጊ ነገሮችን በሚሟላት ለማገልገል እና ለመምራት ኃላፊነትን የሚሸከም ነው።

<u>ደቀመዝሙርነት (ስልጠና) መሪ:</u> የአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ የደቀመዝሙርነት ስልጠና ቡድን የተሰጠውን ደቀመዝሙር የማፍራትን አስመልክቶ የእግዚአብሔርን ዓላማ የማስፈጸም አገልግሎት ድርሻ በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።

<u>ታላቅ ወንድሞች/ ታላቅ እህቶች:</u>በእድሜ የሚበልጡ,የበሰሉ አማኞች ለኢየሱስ እንዴት እንደሚኖር የተማሩ፤ ኢየሱስን ስበክ, ሌሎችም ለኢየሱስ መኖር ይችሉ ዘንድ የሚረዱ ናቸው።አዲስ የዳኑ ወገኖችን

ስለመሰረታዊ የግል ህይወት፤ወንጌል ስብከት፤የቤተሰብ ህይወት፤የቤተክርስቲያን ህይወት፤እና ደቀመዝሙር ስለማድረግ በማስተማር ያገለግላሉ፡፡እንዲሁም ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ የሚመጡትን አማኝ የሆኑ ነገር ግን አዲስ መጪዎችን በመቀበል ያገለግላሉ፡፡አጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ አንድ አካል እንዲሆኑ ይረዷቸዋል፡፡

<u>አዲስ አማኞች</u>:ለኢየሱስ ለመኖር ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ እና በታላቅ ወንድሞች እና እህቶች የተማሩ ናቸው፡፡

<u>ጎብኚዎች</u>: በቡድን ተሰብስበው ነገር ግን የአጥቢያው ህብረት አባል ያልሆኑ ናቸው፡፡ እነሱ ለአገልግሎት እና ለቤተክርስቲያን እድገት ትልቅ እድል ይፈጥራሉ፡፡

**<u>ማስታወሻ: የቤት ለቤት ህብረት አባላት ከአንድ የአገልግሎት ቀጠና የበለጠ ጥቅም ሊሰጡ ይችላሉ፡፡</u>**

8 <u>የአስተዳር ቡድን</u>: የአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ እና የስራ እና ነገርም ጨምሮ ቁሳዊ ፍላጎቶች እና የአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱን ንብረት በተመለከተ ለማሟላት ኃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡ሰዎችን በሁለት የአገልጋይ መሪነት ስፍራ ያካትታል፡፡ሁለቱ ስፍራዎች፡

<u>ሽማግሌዎች</u>: እግዚአብሔር ሽማግሌዎችን ለአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሾሟል፡፡እነሱ ለምዕመናኖቻቸው አካላዊ፤ቁሳዊ፤አዕምሮአዊ፤ስሜታዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ኃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡እነሱ የአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱን የእግዚአብሔር መንግስትን በተወሰነ መልክአ ምድራዊ ስፍራ ላይ ለመመስረት የተሰጣትን ዓላማ ትፈጽም ዘንድ ይረዷታል፡፡እነሱ አጥቢያ ጉባኤውን እግዚአብሔር ለህይወታቸው የሰጠውን ዓላማ ይፈጸሙ ዘንድ ይረዳሉ፡፡

<u>ደያቆናት</u>: በጉባኤ ውስጥ የህብረቱ አባላት የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት ሽማግሌዎችን ይረዱ ዘንድ ተሹመዋል፤በተለይ አካላዊ እና ቁሳዊ ፍላጎቶችን በማሟላት፡፡

<u>የሌላ ቤተክርስቲያን ምዕመናን</u>:ሽማግሌዎችን እና ዲያቆናትን ሊመሩ ይገባል፡፡

# <u>ሐዋሪያዊ የወንጌል ተልዕኮ ቡድን</u>

ሐዋሪያዊ የወንጌል ተልዕኮ ቡድን የሰለጠኑ እና የተደራጁ ከሦስት እስከ አስራሁለት የሚሆኑ ወገኖች የመስራቹን ወንጌል አጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ በሚገኙ አከባቢዎች ይዘው ይወጣሉ፡፡ተመሳሳይ መንፈሳዊ ብስለት ባላቸው ሰዎች ይመራሉ፡፡ሐዋሪያዊ ቡድን ሁልጊዜ አጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ ወጥተው በወንጌል ያተደረሱ ስፍዎች ላይ ቤተክርስቲያን ይመሰርታሉ ወይም የደከሙ ነባር ቤተክርስቲያንን ያበረታሉ፡፡በአዲስ ኪዳን አጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ ውጪ የሚያገለግሉ በርካታ ሰዎች የህብረቱ አባል ነበሩ፡፡

ሐዋሪያዊ ቡድን ሁልጊዜ የሚከተሉትን ባለ አምስት ጥቅል ስጦታ የሰዎች ስብስብ ያካተተ ነው፡

<u>ሐዋሪያ</u> ለወንጌል ተልዕኮ ቡድን የመሪነት እና ክትትል የሚሰጥ ነው፡፡
<u>ነብያት</u> እግዚአብሔር አደገኛ ነገር እና ችግር መኖሩን ሲናገር፤እና ሲያስጠነቅቅ ቃሉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡
<u>ወንጌላዊ</u> ህዝቡን ወደ እውነተኛ ለኢየሱስ ለመኖር የሚደረግ መሰጠት የሚመራ ነው፡፡
<u>መጋቢ</u> ህዝቡ የሚያስፈልገውን በመመልከት ለማሟላት ያስባል፡፡
<u>አስተማሪ</u> ህዝቡን በመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች እና ቃል ይመራ እንዲሁም ያንጻል፡፡

ማስታወሻ: ሐዋሪያዊ ቡድን አባላት ከአንድ የበለጠ አገልግሎት ስጦታ ሊያገለግል ይችላል፡፡

# ቤተክርስቲያን

ከአሁን የበለጠ ለቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግስት ታሰፋ ዘንድ ወንጌል የምትሰብክበት እና በኃይል የምትሄድበት ወሳኝ ጊዜ አልነበራትም፡፡ነገር ግን ይህ አስተዳደራዊ እና የሐይማኖት አስተምዕሮ ልዩነቶችን ካላቆምን አይሆንም፡፡ከእግዚአብሔር ቤት ፍርድ የሚጀምርበት ጊዜ መጥቷል፡፡የሱ ቤተክርስቲያን ያለነውር በሚሄዱ የተገነባ ስብስብ ነው፡፡ያለምንም ሰው ሰራሽ መከፋፈል፡፡

በሚሲሲፒ ባህረ ሰላጤ የባህር ዳርቻ የተከሰተው ካትሪና ጥፋት ቤተክርስቲያን ስላላት ኃይል እና ተጽዕኖ በጣም ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ብዙዎች እረፍት የሚያገኙት ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ነበር፡፡ሰዎች በህብረት ስለ ፍቅር ይሰሩ ነበር፡፡የሰዎች ኑሮ ተነክቶ ነበር ቤተክርስቲያን ስጋዊና መንፈሳዊ ነገራቸውን ስታገለግል ነፍሳት ዳኑ፡፡

ከላይ በተማርከው መሰረት ስለ ቤተክርስቲያን በአዕምሮህ የሳልከው ስዕል እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ትሆን ዘንድ እንደሚፈልገው ይሆን ዘንድ ጸሎታችን ነው፡፡እግዚአብሔር በቡድኑ ውስጥ እንዲኖርህ የሚፈልገውን ድርሻ ደግሞ ትመለከታለህ፡፡ጸሎታችን ዓለምን በወንጌል ትደርስ ዘንድ በልብህ ከእግዚአብሔር ከመሰረታቸው **ቡድን-ቤተክርስቲያን** ጋር አብረህ ለመስራት እንድታቅድ ነው፡፡

መሰረታዊ ጥያቄ: ከሌሎች ከእግዚአብሔር ከመሰረታቸው **ቡድን-ቤተክርስቲያን** ጋር አብረህ ለመስራት ትፈልጋለህን፤እንዲሁም ከቡድኑ ጋር እግዚአብሔር ታገለግል ዘንድ በሚፈልገው ስፍራ ታገለግላህን?

God has a wonderful purpose for your life. We want to help you find and fulfill that purpose. If you would like further training, prayer, or
information on how you can work with others to share Jesus where you live; please contact us.


WRITE TO:

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. BOX 633
Grapevine, TX 76099
U.S.A.

Phone (228) 255-9251

by Email
Send your request to basic@basicministries.com
Or
Visit our web site www.basicministries.com


IF YOU WERE BLESSED BY THIS STUDY SHARE A COPY WITH SOMEONE.
ADDITIONAL COPIES CAN BE DOWNLOADED FROM OUR WEB PAGE
www.basicministries.com.

COPIES ARE AVAILABLE IN OTHER LANGUAGES.
CONTACT US FOR MORE INFORMATION.

HAVE YOU EVER WONDERED WHAT CHURCH IS ALL ABOUT?

WOULD YOU LIKE TO KNOW HOW
TO REALLY BE PART OF THE FAMILY OF GOD?

WOULD YOU LIKE TO KNOW HOW TO
LIVE A CONSISTENTLY SUCCESSFUL LIFE?

WOULD YOU LIKE TO SHARE WITH A FRIEND OR LOVED
ONE ABOUT HOW TO BE PART OF THE FAMILY OF GOD?

!!THEN THIS BOOK IS FOR YOU!!

Compiled by Henry Pulsifer

&

Illustrated by Paula Mingucci

This is one of a series of learning guides designed to help you live a successful, victorious, life. Henry has experienced the victory that comes from living for Jesus for over 60 years; including God's healing from Cancer as he walked with the cross. Since his healing he has traveled the world sharing Jesus and helping others learn how to find victory and success by living for Jesus, and fulfilling God's purpose for their life.

Out of this experience he has compiled several foundational learning guides that enable people to understand and live the basic Bible principles for success and victory in life. This particular learning guide is designed to help you understand what God's Spiritual family The

Church is, what it does, and how to be part of it. It can also be used to help you teach others about The Church, and is appropriate for individuals or groups.

COPYRIGHT 1990 ALL RIGHTS RESERVED
No part of this booklet may be reproduced without permission from the publisher.
Except, portions may be reproduced if distributed free of charge.
Proper credit should be given for the source of the material.

PUBLISHED BY:

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. Box 633
Grapevine, TX76099
USA

Phone (228) 255-9251
Email  basic@basicministries.com
Web page www.basicministries.com